DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# High School Online Application

**ተዘውትረው የሚነሡ ጥያቄዎች (FAQ)፤ ለትምህርት ዓመት 2012-2013 ዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ**

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ ድረ ገጽ መሠረት ያለው በኢንተርኔት የሚቀርብ የ 9ኘኛ እና 10ኛ ክፍል አዲስ መጥ ተማሪዎች በ Banneker ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በ Columbia Heights Education Campus, በ Ellington School of the Arts, በ McKinley Technology ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በ Phelps ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በ School Without Walls ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ **እና** በ Washington Metropolitan ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ለመግባት የሚጠቀሙበት ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ ተማሪዎች ለማመልከት ለሚፈልጉባቸው ትምህርት ቤቶች "በኢንተርኔት አማካይነት" የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ እንዲያስገቡ ይፈቀድላቸዋል።

ጉልህ ጭብጥ እውነታዎች

- ለ 2012-2013 የትምህርት ዓመት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ ወቅት **ኅዳር (November) 21, 2011 ይጀምር እና ጥር (January) 6 ያበቃል።**
- ለማመልከት በምትፈልግባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ ማመልከት የምትችልና ሊቀበሉህ የሚችሉ ትምህርት ቤቶች ቁጥር መጠን ደግሞ ወሰን የሌለው ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ በዚሁ ልክ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ ትምህርት ቤት የሚቀበልህ ለመሆኑ የሚሰጥ ዋስትና አይኖርም።
- ማመልከቻው በኢንተርኔት አማካይነት መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ከዚህ ውጪ በወረቀት ለማመልከት የሚደረግ ጥረት ተቀባይነት አይኖረውም።

1. **የማመልከቱ ሂደት ለምንድን ነው የሚለዋወጠው?**

   የማመልከቱን ሂደት በማቀናጀት እና በኢንተርኔትም እንዲካሄድ በማድረግ፣ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በዲሲፒኤስ ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያቀርቧቸው ዕድሎች ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችሉ ሂደቱን እያቃለልን መሆናችንን ዲሲፒኤስ ያምናል።

2. **ማመልከቻዬን ማስገባት የምጀምረው መቼ ነው?**

   ተማሪዎች በኢንተርኔት አማካይነት የሚያደርጉት የምዝገባውን ሂደት ከ **ኅዳር (November) 21, 2011*** ጀምሮ የመጠቀም እድል ይኖራቸዋል።

3. **ማመልከቻዎች ገቢ የማድረጊያ የመጨረሻው ቀን መቼ ነው?**

   ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መደበኛው ማመልከቻ የማስገቢያ ሂደት **መጨረሻ የማስገቢያ** አንድ ቀን ሲኖር፣ ይኸውም **ጥር (January) 6, 2012***ነው።

   ***Ellington School of the Arts** *የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት፣* ***ታኅሣሥ (December) 15, 2011*** *የቅድሚያ ቀን ይኖረዋል። Ellington እስከ ጥር (January) 6, 2012, ድረስ ማመልከቻዎችን የሚቀበል ሲሆን፣ የቃል ጥያቄ የሚቀርብላቸው በቅድሚያ ማመልከቻ የማስገቢያ መጨረሻ ቀን ማመልከቻቸውን ገቢ ላደረጉ ተማሪዎች ነው ዋስትና የሚሰጠው።*

4. **የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ የሚሠራው እንዴት ነው?**
   - ተማሪዎች ለሚያመለክቱባቸው ትምህርት ቤቶች **አንድ** ማመልከቻ ገቢ የሚያደርጉ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ደግሞ በግል የማመልከቻው ቅጂ ይደርሰዋል።
   - ተማሪዎች የማመልከቻዎቻቸውን ዝግጅት መጀመር፣ የተጀመረውንም ይዘው መጠበቅ እና በኋላም ለማጠናቀቅ ተመልሰው በሌላ ጊዜ መምጣት ይችላሉ። ማመልከቻው ልዩ ትምህርት ወደሚሰጡ ትምህርት ቤቶች "submit" (ገቢ አድርግ) የሚለውን ቁልፍ ተማሪው ጠቁሞ እስከ አልተጫነው ድረስ ማመልከቻው ወደ ልዩ ትምህርት ቤቶቹ አይደርስም።
   - ሁሉም ትምህርት ቤቶች ከፍተው ሊያዩት የሚችሉ የድጋፍ ደብዳቤ ወረቀቶችን፣ መምህራን ሊሞሉ ወይም በኮምፒዩተር ላይ ሊጭኑ ይችላሉ።

- ማመልከቻውን መጨረሻ ማስረከቢያ ቀን **ጥር (January) 6, 2012** ነው።
- ተጨማሪ ቁሳቁሶችን፣ ቃለ መጠይቆችን ወይም የቃል ጥያቄዎች መኖርን ሊጠይቅ የሚችል ሁኔታዎችን ጨምሮ ትምህርት ቤቶች በመደበኛው የመቃኘት እና የምርጫ ሂደት ይራመዳሉ።
- በ **የካቲት (March) 26, 2012**፣ ተማሪዎች የትኛው ትምህርት ቤት እንደተቀበላቸው እና እንዳልተቀበላቸው ለማሳወቅ አንድ የማሳሰቢያ ማስታወሻ ደብዳቤ ይላክላቸዋል። በተጨማሪ፣ ተማሪዎች እና ወላጆች ውጤቶቻቸውን ለማየት በኮምፒዩተር አማካ ይነት መጠቀም ይችላሉ።

**5. ለእያንዳንዱ የግል ትምህርት ቤት ተጨማሪ የትምህርት መሣሪያዎች እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?**
አብዛኛዎቹ እያንዳንድ ገላዊ ትምህርት ቤቶች፣ በኢንተርኔት አማካይነት (Online Application) ማመልከቻ፣ ለማሟላት ተጨማሪ መረጃዎች ያስፈልጓቸዋል። አንድ ጊዜ ማመልከቻውን ከጀመርክ እና ለማመልከትም የምትፈልግባቸውን ትምህርት ቤቶች አንዴ ከመ ረጥክ በኋላ፣ ለእነዚህ ለመረጥካቸው ትምህርት ቤቶች፣ ተጨማሪውን የማመልከቻ ክፍል ማጠናቀቅ ትችላለህ። ስለ እያንዳንዱ ትም ህርት ቤት፣ ስለ አመራረጣ ቸው ሂደት፣ እና እንዲሁም እያንዳንዳቸው እንዲሟሉ ስለሚጠይቋቸው ጉዳዬች ለማወቅ እባክዎን http://dcps.dc.gov/DCPS/commonapp ን ይጎብኙ።

**6. አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቼ ለመማር ከፈለኩ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኢንተርኔት አማካይነት በሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ መጠቀም አለብኝ ወይ?**

ለዚህ ለመጭው የትምህርት ዓመት፣ ለ Anacostia, Ballou, Cardozo, Coolidge, Dunbar, Eastern, H.D. Woodson, Roosevelt, Spingarn ወይም Wilson ትምህርት ቤቶች የምታመለክት ከሆነ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኢንተርኔት አማካ ይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ፣ **መጠቀም የለብህም።** “ከመኖሪያ ክልል ውጪ” ለሆንክባቸው በየትኛውም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለማመልከት እባክህን በክልል ውጪ ሎተሪው ተጠቀም።

**7. በአሁኑ ጊዜ ልጄ Columbia Heights የትምህርት ማዕከል (CHEC) በሚገኘው በ Lincoln መካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስምንተኛ ክፍል ተመዝግቧል። ለ CHEC ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦታ የማግኘቱ ሁኔታ የተረጋገጠለት ነው?**
አዎን። ሆኖም ቦታ የማግኘቱ ምድብ ሁኔታ የተረጋገጠለት ሆኖ እንዲገኝ አሁንም ቢሆን ማመልከቻ ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

**8. ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለ በኢንተርኔት አማካይነት የሚደረግ (Online Application) ማመልከቻ የበለጠ ለማወቅ ከማን ነው መረዳት የምችለው?**

ለበለጠ መረጃ ወይም ስለማንኛውም አሳሳቢ ጉዳይ፣ http://dcps.dc.gov/DCPS/commonapp ይቃኙ ወይም ለ hscommonapplication@dc.gov የኢሜይል መልእክት ይላኩ።